

በነበቸው ፍቅርና  በጋለ የተሐድሶ መንፈስ ተነሳስቶ በበርጋሞና ክረሞና ሰበካዎች የሚገኙ ሎሎች ማኅበራትን ማስተባበር ችለዋል። በመካከላችን ሲኖሩ  ውስጣዊ ሰላም የሚሰጥ፤ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ምሕረት የሚገልጽና  እንደ እርሳቸው ደግ ሰው የመሆን ፍላጎት የሚቀሰቅስ ደስተኛ፤ግልጽና ብሩህ ፈገግታ እያሳዩ አልፈዋል። ስለ ሰማያዊው  ዘላለማዊ ሕይወት በነበራቸው የማያቋርጥ ተስፋ
ዕለታዊ ፈተናዎችን ሁሉ በደስታ የመቀበል ብርታይ ይሰጣቸው ነበር።

እ.ኤ.አ. 1970 ዓ.ም ሰኔ ወር  ለሲስተሮች  በሰጡት አስተምህሮ አጥብቀ የተናገሩት ስለ ፋሲካዊ ደስታና በገነት ከጌታ ጋር ስለሚኖረን  ግንኙነት ነበር።ወደ ሰማይ እየተመለከትን “ያቀን ለእኔም ይመጣል፤ትልቅም ትንሽም
ስቃይ ፤ የፍቅርና  ለእግዚአቢሔር  የመስጠት ተግባሮቼን በፊቱ የማቀርብበት ቀን፤ የነፍስና የስጋ ስቃያችን ሁሉ አንድ ቀን በላይ በሰማይ ልክ እንደ የክርስቶስ  ስቃይ ወደ ደስታ ይለወጣሉ! “ በሰማይ  ወደር የሌለው ዘላለማዊ ደስታና ክብር ሙላት ይኖረናል”! ።  ማድረ ዶዚተያ  እ.ኤ.አ. መስከረም 2ቀን 1970 ንጋት ላይ “እንዴት ደስ ይላል! እንዴት ደስ




ይላል!” የሚል ድምጽ ካሰሙ በኋላ  ጌ.ኢ.ክ በሰማይ የዘላለማዊ ሰርግ ድግስ ተካፋይ እንዲሆኑ ጋበዛቸው። የእርሳቸ አሰካሬን እ.ኤ.አ. ከ1991 ጀምሮ  በበርጋሞ በገዳማችን ጸሎት ቤት ውስጥ ይገኛል። ብዙ ሰዎች
እየጎበኙ ልዩ ልዩ ጸጋ ይጠይቁአቸዋል። ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቸስኮ ሕዳር 25.2021  የመንፈሳዊነት የክብር መዓርግ ሰጡአቸዋል።

## ከማድረ ዶዚተያ ጽሑፎች

የድንግል ማርያም ጸጥታ  እንዴት  ትልቅ ሚስጢር ነው፡ በመልአኩ ብሥራት ጀምሮ   አስተማሪ የሆን ክቡር ሃብት ነው! የትሕትና፤ ራስን የመካድ፤ እግዚአብሔር በእርሷ ለሚፈጸመው ሥራ ሁሉ ክብር የመስጠት  የፍቅር ሚስጢር ነው፡


አርሶላይን ዘንጽ. ድ.ማ. ደናግል ማኅበር
ሽያ ማዞነ 20/A 24121 በርጋሞ(ኢ.ታሊ.)


# በደስታ ለእግዚአብሔር
# የተሰጠ ሕይወት

## የተከበሩ
## ማድረ ማርያ ዶዚተያ ቦታኒ









## የእርሳቸው ሕይወት

ማርያ ዶመኒካ እ.ኤ.አ. ግንቦት 31ቀን 1896 ፒያንካ ዲ ሳን ጆቫኒ ቢያንኮ (በርጋሞ ኢ.ታሊ) ተወለደች።በቤተሰቧና በቁምስና ባገኘቻቸው የሰብአዊና የእምነት እሴቶች ተደግፋ ሕይወቷንና ታላቁ ዓላማዋን ስኬታማ

ለማድረግ በጋለ መንፈስና በተከፈተ ልቦና የወጣትነት ጉዞአን ጀመረች። ማርያ ዶመኒካ ኤንዲነ የሚገኘው አዳሪ ት/ቤት በቆየችባቸው ዓመታት ሁሉ ግልጽ የሕይወት ዕቅድ ነበራት፡ "አምለኬ ሆይ ቅድስት ለመሆን ቃል እገባለሁኝ" እ.ኤ.አ. በ1913 በኦርሶላይን ደናግል ማኅበር ውስጥ በአዳሪ ት/ቤት ቆይታዋ ደስተኛ በሆነ ተግባቢ ጸባይዋ፤ ማራኪ ፈገግታና ደግነቷ በአስተማሪዎችና በተማሪዎች ዘንድ አድናቆትና አክብሮት አግኝታ እንደ ተምሳሌትም ይመለከቷታል። እ.ኤ.አ. በ1919 መዓርግ የመምህርት ዲፕሎማ



ተቀበለች ፡በመቀጠልም የኦርሶላይን ደናግል ማኅበር አባል ለመሆን ልብሰ ምንኩስና በመልበስ ሲ/ር ማርያ ዶዚተያ የቅዱስ ቁርባን የሚል ስም ተሰጣቸው።

ይህ ስም የመስጠት ምንጭና የሕይወት ማእከል ለሆነው ቅ.ቁርባን የነበራቸው ትልቅ ፍቅር ያመላክታል። በፎርመሽን ዓመታት ከጎናቸው ሆኖ የመሩአቸው የፖስቱላነትና የኖቪስ መምህርት የነበሩ የእግዚአብሔር አገልጋይ ማድረ ጆዙዊና ሰገሲ ነበሩ። ሲ/ር ዶዚተያ ስለ እርሳቸው እንዲህ በማለት ይመሰክራሉ። "የኖቪስ አስተማሪአችን እስከ ዕለተ ሞታቸው /እ.ኤ.አ.31.3.1963/ ያሳዩኝ የቅድስና ሕይወት በየቀኑ የሕንጸት ት/ቤት ሆኖልኛል፡ ሁለመናዬን ለልባቸው አደራ እጥል ነበር"። ሲ/ር ዶዚተያ እ.ኤ.አ. ከ1919-1927 በፐያና በኪኞሎ ት/ቤቶች ሲያገለግሉ ባሳዩት፡ የማስተማር፤የማስተባበርና



የመምራት ብቃታቸው፡በት/ቤትና በአስተማሪዎች ዘንት ትልቅ አድናቆትና ዕውቅና አግኝቶአል። በ1927 የጠቅ. አለቃ ጸሐፊ፤ በ1946 የጠቅ.አለቃ ምክትል ከ1952- 1970 የገዳም ጠቅላይ አለቃ ሆኖ አገልግለዋል። በመሪነት ዘመናቸው ቅ.ቁርባን የወንድማማችነትና ወንጌላዊ ምስክርነት ምንጭ መሆኑን በማመን ልዩ ቦታ ይሰጡት ነበር። በዚህ የእኔ ደቀመዝሙሮች መሆናችሁን ሰው ሁሉ ውቃል(ዮሐ.13፡35) ፡

ገዳሙን በመሩባቸው 18 ዓመታት ውስጥ ያከናወኑት ታላላቅ ሥራዎች፡ የዶን ፍራንቸስኮ ድላ ማዶና(1771-1846)ሕየወት፤ የገዳም ምስረታና የሴት ልጅ ሁለንተናዊ ዕድገት መርሀግብር ካሪዚማችን ታሪክ ፤ ካሪዚማችን ከቅ.አንጃላ መሪቺ (1470-1540) መንፈሳዊነት ጋር ያለው ትስስር የሚገልጽ ጥናት እንዲደረግ አነቃቀቶአል።በጣሊያን፤ ኤርትራ፤ ኢትዮጵያ፤ አርጀንቲና፤ በልጅምና እንግሊዚ አዳዲስ ቤቶች ከፍተዋል። የቤ/ክርስትያን መመሪያ ዎችና የጊዜ ምልክቶች በማስተዋል ሲ/ሮችን በፓስቶራልና በተለያዩ የስነዕድገት ዘርፎች አሰልጥኖአል።ለቤ/ክርስትያንና ለድኾች